*የሰ/መ/ቁ. 15551*

*ቀን 29/2/98 ዓ.ም*

*ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ*
*አቶ አብዱልቃድር መሐመድ*
*ወ/ሮ ደስታ ገብሩ*
*አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ*
*ወ/ሪት ሂሩት መለሰ*

*አመልካች፡- ዩናይትድ ቴክኒካል ኢኩፕመንት ኩባንያ*

*ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ሞተርና መሐንዲስነት ኩባንያ*

*ስለ ውል መፍረስ - ህጋዊ ደንብን ያልተከተለ ውል ስለሚፈርስበት ሁኔታ እና የውል መፍረስ በተዋዋይ ወገኖች ላይ የሚያወጣው ውጤት - የፍ/ብ/ህ/ቁ 1716(1)፣ 1815፣ 1816 እና 1817*

*የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የመኪና ሽያጭ ውል ከፈረሠ በኋላ ገንዘቡ ለአመልካች ተመልሶ በመንግስት የተወረሰችዉ መኪና ወደ ጅቡቲ ትመለስ በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የወሰነውን በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡*

***ው ሳ ኔ*** *፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ጅቡቲ ትመለስ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተሸሯል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡*

*-ውል እንዲፈርስ ከተወሰነ በሓላ ተዋዋዮች ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ የሚወሰነው በውሉ ምክንያት የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ካልሆነ ነው፡፡፡*



የሰ/መ/ቁ. 15551

ቀን 29/2/98 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ደስታ ገብሩ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ዩናይትድ ቴክኒካል ኢኩፕመንት ኩባንያ

ተጠሪ፡- የኢዮጵያ ሞተርና መሐንዲስነት ኩባንያ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የጀመረው የአሁን አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪው ላይ ባቀረበው ክሥ መነሻ ነው፡፡

የክሱ ፍሬ ነገር ከሣሽ ላንድክሩዘር መኪና ለመግዛት ፈልጎ ተከሣሽን የመሸጫ ዋጋ ጠይቆ ጥያቄው በተከሣሽ ተቀባይነት በማግኘቱ ተከሣሹ ባቀረበው የመኪና መሸጫ ዋጋ ተስማምተው ከሣሽ ገንዘቡን የከፈለ መሆኑን፤ ነገር ግን መኪናዋ በተከሣሽ ላይሰንስ ጉምሩክ መጋዘን ከገባች በኋላ መኪናዋ በሕገወጥ መንገድ ስለገባች ማውጣት አትችሉም ሲል ጉምሩክ ስለከለከለ ውሉ ውድቅ ሆኖ ገንዘቡን ከነወለዱ እንዲመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሣሽ የአሁን ተጠሪም ቀርቦ ከተከራከረ በኋላ ፍ/ቤቱ ውሉ የተደረገው ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡት ዕቃዎች ሐምሌ 12/1988 ከወጣው ደንብ በኋላ የተደረገ ስለሆነ፤ ውሉም ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1716/1/ መሠረት ፈራሽ ነው፡፡

ውሉ ፈራሽ ነው ከተባለ ደግሞ ውጤቱ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ሁኔታ ሊመለሱ እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁጥር 1815/1/ ስለሚደነግግ በክሥ አቤቱታው ላይ የተመለከተውን ብር 177,184.23 /አንድ መቶ ሰባ ሠባት ሺህ አንድ መቶ ሠማንያ አራት ብር ከሃያ ሦስት ሣንቲም/ የኢትዮጵያ ብር ወይም 26037.36 /ሃያ ስድስት ሺህ

ሠላሣ ሰባት ብር ከሠላሣ ስድስት ሣንቲም/ የአሜሪካን ዶላር ተከሣሽ ለከሣሽ ይክፈል፣ ዳኝነት በታሪፉ ልክ፣ የጠበቃ አበል 15% ልዩ ልዩ ወጪ 100 /አንድ መቶ ብር/ ጨምሮ ለከሣሽ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪም በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረቡ ፍ/ቤቱ የይግባኙን ክርክር መርምሮ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የተሰጠውን የውሣኔ ክፍል በማጽናት ነገር ግን ውሉ ፈርሶ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ይመለሱ ሲባል ከሣሽ ለመኪናው የከፈለው ገንዘብ ይመለስለት ማለት ሲሆን፤ ተከሣሹም ከውሉ በፊት ወደነበረበት ሁኔታ የሚመለሰው በውሉ ምክንያት ከጅቡቲ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው መኪና ወደ ጅቡቲ ሲመለስለት በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት አንዱን ወገን ወደነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ አድርጎ ሌላውን ወገን ባለበት ሁኔታ በመተው የሰጠውን ውሣኔ አሻሽለን ከላይ በተገለፀው ሁኔታ ወደነበረበት ይመለሱ ሲል ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ የሥር ከሣሽ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ሲያቀርብ ተከሣሹም መስቀለኛ ይግባኝ አቅርቧል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ዋናውን ይግባኝ በተመለከተ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር መሠረት የለውም በማለት፤ መስቀለኛ ይግባኙም በሥር ፍ/ቤቶች ተመሣሣይ ውሣኔ የተሰጠበት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9 መሠረት በይግባኝ ደረጃ ሊታይ አይችልም በማለት መዝገቡን ዘግቶ መልሶለታል፡፡

እንግዲህ የሥር ከሣሹ ማለትም የአሁን አመልካች በ25/8/96 ጽፎ ያቀረበው የሠበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መኪናዋ ወደ ጅቡቲ ትመለስ የሚለው ተጨማሪ የውሣኔ ክፍል አፈፃፀሙን የተወሣሠበ ስላደረገውና የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ማረም ሲገባው ማለፉ ሥነ ሥርዓትን የሚቃረን በመሆኑ ይህ ተሻሽሎ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ ይፀናልን በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የማመልከቻ ግልባጭ ለተጠሪው ደረሶ ጥር 19/1997 ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካቹ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ውሣኔ ከሰጠ በኂላ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ለከፍተኛ ፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረባቸው በውሣኔው እንደተስማሙበት የሚቆጠር ነው ለዚህ ችሎት



ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን አላሣዩም፣ ውሉ ሊፈርስ ይገባዋል ሲባል ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ሁኔታ ይመለሱ መባሉም ትክክል ነው አመልካች መኪናውን አልተረከቡም ለሚሉት አስቀድሞ ያለቀለት ክርክር ስለሆነ አሁን ሊነሣ አይገባውምና አቤቱታው ተሠርዞ ተገቢው ኪሣራ ተቋርጦልን እንሠናበት በማለት የተከራከረ ሲሆን አመልካችም አቤቱታውን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ከፍ ብሎ በዝርዝር የተመለከተው ሲሆን ውሣኔ ሊያገኝ የሚገባው ጭብጥ፤ በአመልካችና በተጠሪው መካከል የነበረው የመኪና ሽያጭ ውል ፈርሶ ወደነበሩበት ይመለሱ ሲባል ለአመልካቹ ገንዘቡ እንዲመለስለት ብቻ ሣይሆን ከጅቡቲ ወደብ መጥታ ጉምሩክ መጋዘን ገብታለች የተባለችውም መኪና ወደ ጅቡቲ መመለስ አለባት ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው? አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው የመኪና ሽያጭ ውል እንዲፈርስ በሥር ፍ/ቤቶች በተሠጠው ውሣኔ ላይ አቤቱታ ያልቀረበበት ስለሆነ ይህን ነጥብ መመርመሩ አስፈላጊ አይደለም፡፡ የተጠሪው ክርክር ውሉ ይፍረስ ከተባለ ውጤቱ በፍ/ሕግ ቁጥር 1815/1/ መሠረት ተዋዋዮች ወደነበሩበት ይመለሣሉ ስለሚል በዚህ ሁኔታ መመላለስ ስለአለብን የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሹ ገንዘቡን እንዲያገኝ ከተወሰነ መኪናዋም ወደጅቡቲ እንድትመለስ መወሰኑ ተገቢ ነው ሲል አመልካች በበኩሉ መኪናዋ ወደ ጅቡቲ ትመለስ ከተባለ ውሣኔው ሊፈፀም የማይችል ይሆናል ባይ ነው፡፡

አከራካሪዋ መኪና ከጅቡቲ ወደብ መጥታ ጉምሩክ መጋዘን ከገባች በኂላ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ገብታለች ተብሎ ጉምሩክ ለከሣሽ ሊሰጥ አለመቻሉንና በዚሁ ምክንያት በመንግሥት ስለመወረሷ ራሱ የሥር ተከሣሽ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ካቀረበው ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡

እንግዲህ ምንም እንኳን የፍ/ሕ/ቁጥር 1815/1/ አንድ ውለታ ሲሠረዝ ወይም ሲፈርስ ተዋዋዮችን በተቻለ መጠን ውለታው ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚደነግግ ቢሆንም መኪናዋ ለመንግሥት በውርስ የገባች መሆኑ እየተረጋገጠ ወደ

ጅቡቲ ትመለስ ተብሎ መወሰኑ የተሠራውን ሥራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ ደግሞ የፍ/ሕግ ቁጥር 1816 እና 1817 የፍ/ሕ/ቀጥር 1815 ልዩ ሁኔታ (exceptions) ሆነው መፍትሄ ይሰጣሉ፡፡

ይኸውም በተለይ ለዚህ ጉዳይ ተጠቃሽነት ያለው የፍ/ሕ/ቁጥር 1817/1/ … የተሠራውን ሥራ ለማፍረስ የማይቻል ሲሆን ወይም አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ከፍ ያለ መሠናክል የሚያመጣ ሲሆን የተሰሩት ሥራዎች እንደረጉ ይቀራሉ ይላል፡፡

ይሁንና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ድንጋጌ በሚቃረን ሁኔታ መኪናዋ በመንግሥት መወረሱን እየተረዳ ወደ ጅቡቲ ትመለስ ሲል የሰጠው የውሣኔ ክፍል መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህን ሥህተት እንዲያርም የቀረበለትን ይግባኝ ያለመቀበሉ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 11936 ጥር 26/96 በዋለው ችሎት ዋናውን ይግባኝ በተመለከተ የሰጠው የውሣኔ ክፍል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ ተሽሯል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 216/94 በ24/7/95 በዋለው ችሎት መኪናዋ ወደ ጅቡቲ ትመለስ በማለት የሰጠውን የውሣኔ ክፍል ብቻ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ ተሽሯል፡፡

የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁጥር 492/90 በ4/11/93 በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት በማጽናት ወስነናል፡፡ የውሣኔው ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤት ይድረሰው መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡



የመ/ቁ.16062

ህዳር 19 ቀን 1998 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጎስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

**መልስ ሰጭዎች፡-** ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ

*ከውል ውጭ ስለሚደርስ አላፊነት- ካሣ ስለሚጠየቅበት ክስ- ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ - የፍትሐ-ብሄር ህግ ቁጥር 2143/1/፣ 2143/2/*

መልስ ሰጭ በአቶ ከበደ ኃይሉ ይሽከረከር የነበረና ንብረትነቱ የአቶ አሊ መሃመድ የሆነ ተሽከርካሪ ሰኔ 5 ቀን 1984 ዓ.ም ባለቤቴን ገጭቶ ገድሏል በማለት እርሷና ሁለት ህፃናት ልጆቿ ተቋርጦብናል የምትለውን ገንዘብ በማስላት ብር 222,000 እንዲከፈላት መስከረም 4 1992ዓ.ም ባቀረበችው ክስ አመልካች ለተሽከርካሪው በሰጠው መድን በጣልቃ ገብነት በመግባት ክሱ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143/2/ መሰረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረበውን ክርክር የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውድቅ አድርጎ በፍሬ ነገሩ ውሳኔ በመስጠቱና ውሳኔውም በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

**ውሳኔ፡-** የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያጸናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. የፍ/ብህ/ቁ.2143 ከውል በሚደርስ አላፊነት የቀለብ ገንዘብ በመጠየቅ በሚቀርብ ክስ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. ሚስት ከውል ውጭ በባሏ ላይ በሚደርስ የሞት ጉዳት የቀለብ ጥያቄ ለማቅረብ ስትል ሚስትነቷን ለማረጋገጥ በፍርድ ቤት የምታቀርበው ጥያቄ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 የተደነገገው የይርጋ ጊዜ አያቋርጥም፡፡